# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ሠነዶች፡-** ACA, BBB, GBA, GBB-RA, GCA-RA, GCB, GJA-RA, GMD-RA, GMG-RA, GKA-RA, HDA, HDB, HDC

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-**የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

## የላቀ ውጤታማ የሥራ ግብረሃይል

**A. ዓላማ**

የላቀ የስራ ግብረኃይል እንዲኖር እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቀልጣፋ የሆነ ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ስልታዊ እና ቀጣይነት ያለው የሥራ ግብረኃይል ሙያዊ እድገት ሂደቶችን ለመመስረት እና የሙያ እድገት ስርዓትን ሶስት ቁልፍ ተግባራት እንደሚከተለው መግለፅ ነው፡-

1. አዳዲስ ሰራተኞችን ከድርጅቱ ጋር ማስተዋወቅ፣ ስልጠና መስጠት፣ እና ሰራተኞች የተመደቡበትን ስራቸውን እንዲሰሩ እና ባሉበት የስራ መደባቸው ላይ ለሚኖሩ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምላሽ መስጠት መቻላቸውን መገምገም፣

2. የሰራተኞችን የሙያ ትምህርት ፍላጎቶች ማጎልበት እና ሰራተኞች አዳዲስ ብቃቶችን እንዲያዳብሩ እና በእቅድ እና ለሙያ እድገት በሚያዘጋጃቸው ሙያዊ ትምህርት የአመራር ዕድሎች ፍላጎት እንዲኖራቸው ማበረታታት፣ እና

3. የግለሰቦች የስራ አፈፃፀም የሚጠበቅባቸውን ብቃት እና ደረጃዎችን ሳያሟላ ሲቀር የተዋቀረ፣ ወቅታዊ እና ውጤታማ ምላሽ እና እርማት መስጠት።

**B. አቋም**

1. የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ዋና አላማው ሁሉም ተማሪዎች እንዲያድጉ እንዲበለጽጉ ማዘጋጀት መሆኑን ያረጋግጣል። የቦርዱን ዋና አላማ ለማሳካት መሰረቱ ሰራተኞቹ ናቸው – ሰራተኞች በየቀኑ የሚያከናውኑት ተግባር ተማሪዎችን እንዲማሩ እና እውቀታቸውን እንዲያበለጽጉ ያዘጋጃቸዋል፤ እንዲሁም ለተማሪዎች እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰብ ትምህርት፣ ደህንነት፣ እና ስኬት የላቀ አስተዋፅኦ ያደርጋል።
   a) የቦርዱ መከባበር የሠፈነበት ባህል የሁሉም ሰራተኞች እና የተማሪዎች ከፍተኛ የስራ አፈጻጸም የላቀ ደረጃ ያለው የትምህርት ማህበረሰብን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ይገነዘባል።

   b) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሁሉም የስራ መደቦች ላይ ያሉ ሰራተኞች፣ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ የእለት ተእለት ግንኙነት፣ የዓመታት ልምድ፣ የጋራ ባህርይ/ገፅታ ወይም ልዩነቶች ምንም ይሁን ምን ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ የማዘጋጀት የጋራ ተልእኮ አላቸው።

   c) ቦርዱ ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያዘጋጇቸውን በግልም ሆነ በቡድን ለህዝብ ትምህርት ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችን እውቅና ይሰጣል።

2. ቦርዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ላለው ተቋማዊ ጥንካሬና ቁርጠኝነት ያሉት ጠንካራ ሰራተኞች መሰረት መሆናቸውን ያረጋግጣል።

   a) ቦርዱ ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ የሁሉንም ሰራተኞቻችንን የተለያየ እውቀት እና ልምዶችን የሚያሳትፍ እና የሚጠቀም በሙያ የበለፀገ ማህበረሰብን ለመገንባት ይፈልጋል።

   b) የሰራተኛ ብቃት ሲጨምር እና የመሪነት አቅም እንዲጎለብት ሲደረግ ግለሰቦች እና MCPS በአጠቃላይ ለማይታወቁ ወይም ፈታኝ ለሆኑ ሁኔታዎች በብቃት እና ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ምላሽ መስጠት፣ በጽናት መቆም እና ተባብረው መስራት ይችላሉ።

3. ቦርዱ እና MCPS በቦርድ ፖሊሲ ACA አድሎ አልባ፣ ፍትሃዊ፣ እና የብቃት ባህልድንጋጌ መሠረት፥ ሰራተኞችን በፍትሃዊነት እና በአክብሮት በመገምገም ስለ ፍትሃዊነት እና አድሎ አልባነት ቀጣይነት ባለው ቁርጠኝነት ያረጋግጣሉ። ቦርዱ ከታወቁት ከእያንዳንዱ የሰራተኛ ማህበራት ጋር በመተባበር ስለ ሰራተኞች የሙያ እድገት ስርዓቶችን በማዘጋጀት ከትንሽ እስከ ከፍተኛ የሥራ ብቃቶችን፣ የአፈጻጸም ደረጃዎችን፣ እና የግምገማ መመዘኛዎችን የመደራደር ተግባር ያከናውናል።

### C. የአተገባበር ስልቶች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በዚህ ፖሊሲ መርሆዎች የሚመሩ የሙያ ማዳበር/ማገልፀግ ስርዓት-አቀፍ ስልቶችን ያዘጋጃል እና ለትግበራ አስፈጻሚ ሀላፊነቶችን ይመድባል።

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አመራር እና ሱፐርቫይዘሮች ዘንድ እና በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች መካከል ስለ ወቅታዊ እና ውጤታማ ሙያዊ ትምህርት፣ ድጋፍ፣ እና ግምገማ ከሰራተኞች የሚጠበቀውን ከፍተኛ የሥራ ብቃት ለማቀናጀት በሚከተለው መልኩ የጋራ ሃላፊነት ሊኖር ይገባል፦

   a) የሱፐርቫይዘሮችን የአመራር ችሎታ ለማዳበር ሙያዊ ትምህርት መስጠት፣ የሱፐርቫይዘሮችን ደህንነት ማሻሻል፣ እና ሱፐርቫይዘሮች በትምህርት ላይ ያተኮረ ክትትልን፣ ለሰራተኞች ቀጣይነት ያለው ግብረመልስ እንዲሰጡ እና እንደአግባቡም ለሰራተኛ ድጋፍ ሰጪ መርጃዎችን እንዲያገኙ ማበረታታት።

   b) በመልካም አቀባበል እና ሁሉንም አዲስ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን እና በአዲስ የስራ መደቦች የተመደቡ ሰራተኞችን ለስኬታማነት እንዲዘጋጁ ሚና-ተኮር እውቀት እንዲሁም ስርአት አቀፍ ደንቦችን የማክበር ስልጠና መስጠት እና ትምህርታዊ ግንኙነቶችን እና ትብብርን ውጤታማ በሆነ መንገድ በማቀናጀት፣ በማስጠናት፣ በማማከር፣ በአሰልጣኝነት ወይም በሌሎች ቴክኒኮች እንደአግባቡ እንዲዘጋጁ ማድረግ።

   c) ለሕዝብ ትምህርት ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የላቀ አስተዋጾ በማበርከት ሁሉንም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያዘጋጇቸውን ግለሰብ ሠራተኞችንም ሆነ በቡድን የሚሰሩትን እውቅና መስጠት።

   d) ሰራተኞችን መገምገም እና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት፣ አስፈላጊ የሥራ ብቃቶችን እና የስራ አፈጻጸም ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ ግብረመልስ መስጠት።

   e) ወደፊት ጥቅም ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ መገልገያዎች/ሪሶርሶች እና በግምገማ ሂደቶች ውስጥ በተዘዋዋሪ የሚፈጸሙ ማንኛውም አድሎአዊ አሰራሮች ላይ ግንዛቤን ለማሳደግ እና የዚህ ዓይነቱ

ምግባር MCPS ውስጥ እንዳይቀጥል ለማድረግ ሁሉን አቀፍ፣ ባህልን ባከበረ መልኩ ምላሽ ሰጪ የሆነ ሙያዊ ትምህርት መስጠት እና ተግባራዊ ማድረግ።

2. ሁሉም ሰራተኞች፣ የስራ ድርሻቸው ምንም ቢሆን፣ ወይም ለዓመታት ያከማቹት የሥራ ልምድ ቢኖራቸውም፣ ሙያዊ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሳድጉ፣ አዳዲስ የሥራ ብቃቶችን እንዲያዳብሩ፣ እና ወደ ሙያዊ የስራ እድገት የሚያመሩ የአመራር ዕድሎችን እንዲጠቀሙ እና እንዲበረታቱ መደረግ አለባቸው። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚከተሉትን ለማከናወን የአሰራር ሂደቶችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል –

   a) ሁሉም ሰራተኞች ሙያዊ ፍላጎቶችን እንዲያሳድጉ፣ አዳዲስ የሥራ ብቃቶችን እንዲያዳብሩ እና በየግላቸው ቀጣይነት ላለው የሙያ ትምህርት ዕቅዶች የአመራር ዕድሎችን ለመሻት አዳዲስ እድሎችን በንቃት ማዳበር፤

   b) እነዚህ እቅዶች ከፋይናንስ አንጻር አግባብ የሆነ እና ለ MCPS ተልዕኮ እና ለስቴት የሙያ ማረጋገጫ መስፈርቶች ተገቢ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መገልገያዎችን/ሪሶርሶችን ተደራሽ ማድረግ፤

   c) ተመሳሳይ በሆኑ የሙያ ትምህርት ዘርፎች የሚገኙ ማህበረሰቦችን ለማበረታታት፣ እና በተቻለ መጠን ለተለያዩ የስራ መደቦች አግባብ በሆነ መልኩ ሰራተኞችን ለመመደብ ከሰው ሀብት እና ልማት ጽ/ቤት/Office of Human Resources Development ውጪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች የሚከናወኑ የትምህርት እድሎችን ማስተባበር፤ እና

   d) ስለ ሙያዊ ይዘቱ፣ ንድፍ/ዲዛይን፣ እና ተዛማጅነት መኖሩን ለማረጋገጥ የሰራተኞችን አስተያየት መገምገም –

      i. ስለ ሙያዊ ትምህርት በሕግ፣ በፖሊሲዎች፣ ወይም በመመሪያ ላይ የተደነገጉ መስፈርቶችን ለማሟላት

      ii. ሚና-ተኮር ሙያዊ ትምህርት ያስፈልጋል፣ እና

   e) ሰራተኞች በተደጋጋሚ የሚለቁባቸውን የሥራ መደቦች መረጃን መሰረት በማድረግ ለመሙላት አስቸጋሪ የሆኑ የስራ መደቦችን በመለየት እንዲሁም ሌሎች ድርጅታዊ ፍላጎቶችን በመለየት ሰራተኞችን በማበረታታት እና በማዘጋጀት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለእነዚህ የስራ መደቦች እንዲያመለክቱ ስልታዊ ዕቅዶች በማዘጋጀት ስልጠና እና የክህሎት ማጎልበት መስጠት በእነዚህ ክፍት የስራ መደቦች ላይ የአመልካቾችን ቁጥር መጨመር።

3. በዝርዝር የተቀመጡ መሰረታዊ ብቃቶችን ወይም የአፈጻጸም ደረጃዎችን የማያሟሉ ሰራተኞችን የሚመለከቱ የማስተካከያ ጣልቃገብነት እርምጃ ፕሮቶኮሎችን ለማዘጋጀት MCPS ከእያንዳንዱ የሰራተኛ ማህበር ጋር በትብብር ይሠራል።

   a) የሥራ አፈጻጸም ማሻሻያ ሂደቶች አግባብነት ባለው መልኩ በበርካታ የመረጃ ነጥቦች ላይ በመመስረት እንደ አስፈላጊነቱ በተቻለ መጠን ከስራ ጋር የተያያዙ ዝቅተኛ የሥራ አፈፃፀም ሁኔታን የመፍታትና ስልቶችን የመለየት ተግባርን ያካትታሉ።

   b) ከሚጠበቀው በታች ለሆነ አፈጻጸም መፍትሄ ለመስጠት ወይም ወደ ድጋፍ አገልግሎቶች ለማስተላለፍ የአፈጻጸም ማሻሻያ እቅዶች፣ እንደ አስፈላጊነቱ እገዛ እና ግምገማን ሊያካትቱ ይችላሉ። አማራጮች የቴክኒክ እውቀትን ለማሻሻል የተቀናጀ ድጋፍን ለመስጠት ወይም አስፈላጊ

የሆኑትን እርምጃዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሰራተኛን እንደገና ማሰልጠን ወይም እንደገና መመደብን ሊያካትቱ ይችላሉ።

4. ሚስጥራዊ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰራተኛ እርዳታ ፕሮግራም ሊኖር ይችላል–

   a) በግለሰብ እና በቡድን ድጋፍ በሚሰጡ የሙያ መማር እድሎች የሰራተኞችን ችሎታና ብቃት ማሳደግ፣ እና

   b) ጤናማ የስራ አካባቢን ለማጎልበት እና በስራ ቦታ ላይ ሊታዩ የሚችሉ ስጋቶችን በአፋጣኝ እና ውጤታማ በሆነ የግጭት አፈታት ዘዴ ስልቶችን በመተግበር የሥራ ግብረሃይል ትብብርን እና ድርጅታዊ ጥንካሬን ማሳደግ።

## D. የሚጠበቁ ውጤቶች

1. MCPS ከፍተኛ ብቃት ያላቸው እና በጣም ጥሩ የሙያ ብቃት ያላቸው የሰው ሃይል መሳብ፣ መቅጠር፣ ሙያ ማዳበር እና በሥራ ላይ ማቆየት አለበት፣ ይህም የሚከተሉትን የሚያሟሉ ሰራተኞችን ያካተተ መሆን አለበት –

   a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን ቀጣይነት ያለው የላቀ፣ ፍትሃዊ፣ እና አድልዎ አልባ አሠራርን ቁርጠኝነት በተግባር ማረጋገጥ፤

   b) ለሁሉም ተማሪዎች፣ ለባልደረቦቻቸው፣ እና ለሚያገለግሉት ማህበረሰብ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ማስተናገድን፣ ታማኝነትን እና አክብሮትን የሚያሳዩ እና የሚለማመዱ፣ እና

   c) MCPS ውስጥ በሁሉም የስራ መደቦች ላይ ያሉ ሰራተኞች፣ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የዕለት ተዕለት ግንኙነት፣ የስራ ልምድ፣ አንድ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ወይም ልዩነቶቻቸው ምንም ይሁን ምን፣ ሁሉም ተማሪዎች በእውቀት እንዲበለጽጉ የማዘጋጀት የጋራ ተልዕኮ እንደሚጋሩ እና ለዚያም ተልዕኮ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ በየጊዜው የሚያረጋግጡ።

2. MCPS ብቃቱ እና የአመራር አቅሙ በቀጣይነት እና ወጥ በሆነ መልኩ በሚበረታታ እና በሚደገፍ እጅግ ጥሩ በሆነ የሰው ሃይል አማካኝነት አዳዲስ ሀሳቦችን/ዘዴዎችን በመጠቀም ለውጥ ማምጣት፣ በትብብር መስራት፣ እና የፈጠራ ችሎታን እና ድርጅታዊ ጽናትን ማሳየት አለበት።

## E. ክለሳ እና ሪፖርት

ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ነው።

**ተዛማጅ ሠነዶች፡** ANN CODE ED 6-202-6-203, Code of Maryland Regulations 13A.07.06 and .08

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** የፀደቀው በውሳኔ ቁጥር 248-05 ሜይ 10, 2005 ሲሆን እንደገና በውሳኔ ቁጥር 130-25 ማርች18, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Compliance and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Division of Specialized Support Services,<br>School Counseing Services Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity an Organizational Development, Student Compliance and Appeals<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481,1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024